Week 29

Grade 2

# ብልኂ ሴት



Leveled

# ብልኂ ሴት

Leveled | Grade 2 | Week 29



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2008 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



በባለቤቷ ባህርይ የተቸገረች
አንዲት ሴት ነበረች::



ሴት አያቷን ምክር ጠየቀች።



አያቷም የአንበሳ ጋማ እንድታመጣ ነገሯት።
ለማምጣት ፈቃደኛ ሆነች።



አንበሳውን እንዴት መቅረብ እንዳለባት ዘዴ ቀየሰች::



ከዚያም ስጋ ይዛ ሄደች።
ለአንበሳው በርቀት
ወረወረችለት።



በቀጣዩ ቀን ቀረብ ብላ ወረወረች።



አንበሳው ለመዳት:: በቀላሉ
መቅረብ ቻለች::



ጋማውንም መቁረጥ ቻለች፡፡

ወደአያቷ ይዛ ሄደች፡፡

አያቷ በጣም ተደሰቱ፡፡



“አንቺ ጎበዝ ሴት ነሽ፤ አንበሳ በጣም ኃይለኛና የማይለመድ እንስሳ ነው። ባለቤትሽ የአንበሳውን ያህል አያስቸግርሽም፤ ወደቤትሽ ሂጂ” አሏት።



አንድታሰተውል ሰለረዷት
አያቷን አመስግና ወደቤቷ
ሄደች::



ከዚያም ከባለቤቷ ጋር የሚያቀራርባትን ነገር ማድረግ ጀመረች::

እሱም አጸፋውን መለሰ::



ባልና ሚስቱም ተስማምተው መኖር ጀመሩ::
የአያቷን ምክር በመቀበሏም ተደሰተች::